CNCM SOCIETY OF ETHIOPIA

EIPA

EMCCMO
ETHIOPIAN MUSIC COPY RIGHTS & NEIGHBOURING RIGHTS COLLECTING MANAGEMENT ORGANIZATION

# የጋራ አስተዳደር ማህበራት ስምምነት የፕሬስ መግለጫ

**በኢትዮጵያ የቅጂና ተዛማጅ መብቶች የጋራ አስተዳደር ማኅበር እና በኢትዮጵያ የሙዚቃ የቅጂና ተዛማጅ መብቶች የጋራ አስተዳደር ማኅበር መካከል የጥበብ ሥራዎች የሮያሊቲ ክፍያ የሚፈጸምበት ሥርዓት ላይ የተደረሰ ስምምነት በተመለከተ የተሰጠ የጋራ መግለጫ፡፡**

በሀገራችን የቅጅና ተዛማጅ መብት የተጎናጸፉ የሰው ልጅ የእዕምሮ ውጤት የሆኑ የሥነ-ጽሁፍ፣ የኪነጥበብ እና ተመሳሳይ የፈጠራ ስራዎች ያለ መብት ባለቤቱ ስምምነትና ያለምንም ክፍያ በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ፣በትራንስፖርት ድርጅቶች፣በምሽት ክበቦች፣ በልዩ ልዩ መዝናኛ ቤቶች፣ ወዘተ ለህዝብ አገልግሎት በመቅረብ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚሁ ምክንያት የፈጠራ ሥራ ባለቤት የሆኑ ባለሙያዎችና ተቋማት ከዘርፉ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም ካለማግኘታቸውም በተጨማሪ በቅጅ መብት ጥበቃና ልማት ስራዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደሩ ይገኛሉ፡፡ የፈጠራ ክህሎትና ተሰጥዖ ባላቸው ሰዎች ድካምና ጥረት የተገኙ የፈጠራ ስራዎች በሂደቱ ምንም ተሳትፎ ባልነበራቸው እና በሌላቸው ሰዎች መጠቀሚያ ሲሳይ ሆነው ቆይተዋል፤ አሁንም እየሆኑ ይገኛሉ፡፡

በ1996 ዓ.ም የወጣው የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 410/1996 በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ እንዲቻል ተግባራዊ

የተደረገ ቢሆንም የፈጠራ ሥራ ባለቤቶችን መብትና ጥቅም ከማስከበር አንጻር ክፍተቶች የነበሩበት በመሆኑ የታለመለትን ግብ በተሟላ መልኩ ለማሳካት አልተቻለም፡፡ በተለይም ባለመብቶች ሥራዎቻቸውን በጋራ በማስተዳደር የኢኮኖሚና የሞራል መብቶቻቸውን የሚያስከብሩበት ስርዓት በአዋጁ ውስጥ አለመካተቱ ተጠቃሽ ክፍተቶች ነበሩ፡፡

በዚሁ ምክንያትም በ1996 ዓ.ም የወጣውን 410/1996 የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ክፍተቶች የሚሞላ የማሻሻያ አዋጅ 872/2007 በ2007 ዓ.ም እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ ይህ የማሻሻያ አዋጅ በዋናነት የፈጠራ ሥራ ባለቤቶች መብቶቻቸውን በተደራጀና በተጠናከረ አግባብ ማስተዳደር የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር፣ ስለቅጅና ተዛማጅ መብቶች የጋራ አስተዳደር ማህበር አመሠራረት፣ አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት፣ ስለ ሮያሊቲ ክፍያ ሥርዓት የመሳሰሉትን አካቶ ተደንግጓል፡፡ይሁን እንጂ የማሻሻያ አዋጁ ሥራ ላይ ቢውልም በጋራ አስተዳደር ማህበራት መካከል በነበረ የተናጠል አካሄድ፣ የሚመለከታቸው አካላት ትብብር ማነስና ተያያዥ ምክንያቶች ላለፉት ዘጠኝ አመታት በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ ሳይሆን ቆይቷል፡፡

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን አዋጁን ተፈፃሚ በማድረግ የፈጠራ ሥራ ባለቤቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ የበኩሉን ጥረት ሲያደርግ ቢቆይም ከላይ በተጠቀሱት እና በሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች በሚፈለገው ደረጃ ወደፊት መጓዝ አልቻለም፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን

አዲስ  የአመራርና አሰራር ስርአት በመቀየስ ከሁለቱ የጋራ አስተዳደር ማህበራት ቦርድ ሃላፊዎች ጋር ለወራት የዘለቀና የትብብር ሁኔታን የሚያጎለብቱ የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት እንዲሁም ለሁለቱም ማኅበራት ሙያዊ እገዛ በማድረግ በልዩ ሁኔታ በመሥራቱ መልካም ውጤት ለማየት ተችሏል፡፡ ይህን አብሮ የመሥራት ፍላጎት ተከትሎም ሁለቱ የጋራ አስተዳደር ማህበራት ወጥ የሆነ የሮያሊቲ ቀመር በማዘጋጀት ሮያሊቲ ለመሰብሰብ እና ለማከፋፈል ከስምምነት ደርሰዋል፡፡ በዚህም አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግና ለአመታት በተስፋ ሲጠባበቁ ለቆዩ ባለመብቶች ተጠቃሚነት መረጋገጥ እና ለጥበብ ዘርፉ አጠቃላይ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማበርከት ወደሚያስችል አዲስ ምእራፍ የምንሸጋገርበት ሁኔታ ላይ እንድንገኝ አስችሎናል፡፡ ይህ ስምምነት የፈጠራ ሥራዎች ባለቤት ሆኖ ነገር ግን ከፈጠራ ሥራዎች ምንም አይነት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሳያገኝ ለቆየው የፈጠራ ሥራ ባለቤት ወይም ባለሙያ እፎይታን የሚሰጥ፣ የዘመናት ጥያቄዎቹን የሚመልስ፣ ለተጨማሪ ፈጠራ የሚያበረታታውና አጠቃላይ በዘርፉም ላይ መነቃቃት የሚፈጥር ትልቅ እርምጃ ነው፡፡ በዚህ ዘርፉ ዙሪያ ላሉ አካላትና ለመንግስትም ትልቅ ዜናም ነው፡፡

በመሆኑም  የሮያሊቲን ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ማሻሻያ አዋጅ 872/2007 አንቀጽ 34(1) ላይ እንደተደነገገው ጥበቃ የሚደረግላቸውን ስራዎች ከሚጠቀሙ አካላት ሮያሊቲ መሰብሰብና መብት ላላቸው የፈጠራ ሥራ ባለቤቶች ማከፋፈል

የጋራ አስተዳደር ማህበራቱ ስልጣንና ተግባር በመሆኑና ሁለቱም የጋራ አስተዳደር ማህበራት በአንድ የሮያልቲ ቀመር ስርአት በጋራ ለመሥራት የተስማሙ በመሆናቸው በአዋጁ በተደነገገው መሠረት የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ያላቸውን ሥራዎች ለንግድ አላማ ወይም ለሥራዎቻቸው እንደ ግብዓት የሚጠቀሙ አካላት ጥቅም ላይ ላዋሉት የፈጠራ ሥራ ተገቢውን የሮያልቲ ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለባቸው።

የአዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን በማህበራቱ የጋራ ኮሚቴ የተዘጋጀውን የሮያሊቲ ቀመር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተለይም ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን እና የብሮድካስት ድርጅቶች ጋር ውይይት በማድረግ እና በባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ የጸደቀውን የሮያልቲ መጠን ተቀባይነት እንዲያገኝ በማድረግ አሠራሩ ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገራችን ሥራ ላይ እንዲውል የአዲስ ታሪክ ጅማሮን ያበሥራል።

የጥበብ ኢንዱስትሪው ለውጥ ለሀገር ሁለንተናዊ እድገት ያለው ፋይዳ የማይተካ በመሆኑ አዋጆችን እና አሠራሮችን ሥራ ላይ በማዋል ለመደገፍ ጥረት እየተደረገ ነው። ከዚህ ደግሞ ቀዳሚው የሮያልቲ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ ነው። ይህ የሮያልቲ ሥርዓት የፈጠራ ሥራ ባለቤቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ለተጨማሪ የፈጠራ ሥራ በማበረታታት አጠቃላይ የባህል ኢንዱስትሪው ላይ ያለውን እድገት በማፋጠን በጎ ተጽዕኖ ያሳድራል። ከዚህ በተጨማሪ የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር ያደርጋል፣የቴክኖሎጂ

እድገትን በማፋጠን የማህበረሰብን የኑሮ ሁኔታ በማዘመን ያሻሽላል፣ በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ከብዙ መስኮች በሚመነጨው የፈጠራ ስራዎቻቸው ተጠቃሚ እንዲሆን ያስችላል፡፡ይህ ዘርፍ ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ እድገት ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑና በሀገራችንም ከጠቅላላ ሀገራዊ ምርት ከአራት በመቶ (GDP 4.5%) በላይ የሚያበረክት በመሆኑ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

ስለሆነም ይህ የጋራ ስምምነት የኢንዱስትሪውን ዕድገት ወደ አዲስ ምዕራፍ ለማሸጋገር በሚያግዝ መልኩ ለመስራት መዘጋጀት የሁሉም ባለድርሻ አካላት ግዴታ በመሆኑ የፈጠራ ሥራን ለግል ሥራዎቻቸው የሚጠቀሙ አካላትም በሕጉ መሰረት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡